**ORIGINAL ARTICLE**

# የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ፍተሻ፤ በ2004ዓ.ም. ተሻሽሎ በታተመው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ መነሻነት

**አማረ ተሾመ ሙላቱ (ዶ/ር)[1]**

## *Abstract*

*The main purpose of this study is to examine the approach and organization of grammar content in the eleventh grade Amharic language textbook, published in 2004 Ec. To achieve this objective, the study followed a descriptive research design, as textbooks and contents were selected via purposive sampling technique. Based on the basic questions posed by the study and the theories put forward by the scholars in the field, data were collected through document analysis. The collected data were analyzed using a qualitative method. The Findings show that the grammar content in the textbook has been presented both in deductive and inductive approaches. Inductive approach has shown that there are exercises that are presented only in the form of questions-- questions that require clarification. The grammar content that is presented through the product-oriented and process-oriented approach is included in the textbook. This shows that the role of the students in examining the grammatical content in context is limited. On the other hand, the target text book evaluated in terms of sequence and continuity.  In terms of sequence, a few grammar lessons are arranged sequentially. In contrast, the grammar content in the textbook has been somewhat standardized. In general, the textbook indicates that there are some strengths and weaknesses in terms of approach and organization.*

**Keywords:** *Grammar, content, approach, and organization*

## አህጽሮተ ጥናት

**የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በ2004ዓ.ም ታትሞ ስራ ላይ በዋለው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረባቸው እና አደረጃጀታቸውን መፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም ዋነኛ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ አይነታዊ ገላጭ ንድፍን የተከተለ ሲሆን፣ መማሪያ መጽሐፉ እና ይዘቱ በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ ጥናቱም ካስቀመጣቸው መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች በመነሳት እንዲሁም በመስኩ የሚገኙ ምሁራን የሚያስቀምጧቸው ንድፈ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ እንዲሰበሰቡ ተደርገዋል፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመከተል ተተንትነዋል፡፡ የተገኙ ውጤቶችም እንደሚያሳዩት፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ**

*1.* ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል
*Email: amare.teshome47@gmail.com*

***This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.***
**DOI*: https://doi.org/10.20372/erjssh.2022.0802.05***

ከጥቅል ወደዝርዝር እና ከዝርዝር ወደጥቅል አቀራረብ ተዘጋጅተው እንደቀረቡ ለመለየት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ከዝርዝር ወደጥቅል ከቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ፣ ጥያቄዎቹ ማብራሪያን የሚፈልጉ ሆነው እያለ በጥያቄ መልክ ብቻ የቀረቡ መልመጃዎች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተቃኝተው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ በአብዛኛው ግን የሰዋስው ይዘቶቹ ውጤት ተኮር አቀራረብ ስልትን የተከተሉ እንደሆነ ለመለየት ተችሏል፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በአውድ እንዲፈትሹ ከማድረግ አንጻር ያለው ሚና ውስን እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል መማሪያ መጽሐፉ ከተከታታይነት አንጻር ሲታይ ጥቂት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው እንደተደራጁ፣ በአንጻሩ ከተለጣጣቂነት አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው ይዘቶች በተወሰነ መልኩ ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቢሆንም፣ የአደረጃጀት ቅደም ተከተል መፋለስ እንደሚስተዋልባቸው ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ መማሪያ መጽሐፉ ከአቀራረብ እና ከአደረጃጀት አንጻር በጠንካራ እና በደካማ ጎን ሊነሱ የሚችሉ ዝርዝር ጉዳዮች እንዳሉ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

ቁልፍ ቃላት፡- ሰዋስው፣ ይዘቶች ፣ አቀራረብ እና አደረጃጀት

## 1. መግቢያ

ከቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሰዋስው ነው፡፡ ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ እስከ ሀረግ አመሰራረት ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ እንደሆነ ባየ (2000) ይገልጻሉ፡፡ በሌላ መልኩ Richards & Schimdit (2002) እንደሚያስረዱት ሰዋስው፣ ቃላት እየተዋቀሩ ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበትን ህግጋት እና ተግባር የሚያጠና ነው፡፡ ከሁለቱ ብያኔዎች መረዳት የሚቻለው ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ከድምጽ እስከ ዓ.ነገር ያሉትን መዋቅሮች ከነተግባራቸው ጭምር የሚያጠና መሆኑን ነው፡፡

Ur (1988) ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ በይበልጥ ለማጎልበት የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፣ ሰዋስዋዊ ሥርዓቶችን እና ህግጋትን ተማሪዎቹ በሚፈለገው መልኩ መማር ከቻሉ የታላሚውን የቋንቋ ህግጋት በሂደት እንዲለዩ አስተዋጽኦ ያደርግላቸዋል፡፡ ይህንንም የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ ጌታሁን (1997) እንደሚያጠናክሩት "የቋንቋ ትምህርት ኣላማ ትኩረት በክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓትም ላይ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም አንድን ቋንቋን ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸውና" በሚል ያስረዳሉ፡፡ ከነዚህም ዕሳቤዎች መረዳት የሚቻለው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

የተለያዩ ምሁራን፣ ዓላማንና የትኩረት አቅጣጫን መሰረት በማድረግ የሰዋስው ዓይነቶችን በተለያየ መንገድ ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም፡- ገላጭ ሰዋስው፣ ጥንታዊ ሰዋስው፣ ለዋጫዊ ሰዋስው፣ አገልግሎታዊ ሰዋስው፣ ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው፣ ወዘተ… በሚል ያስቀምጧቸዋል፡፡ ከእነዚህ የሰዋስው ዓይነቶች ውስጥም ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንዱ ነው፡፡ ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው፣ ትምህርታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ዓላማ በማድረግ ስለቋንቋ ማስተማር፣ የሚያጠና የሰዋስው ዓይነት ነው፡፡ እንደ Richards & Schimdit (2002) አገላለጽ ይህ የሰዋስው ዓይነት፣ የአንድን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ትንታኔ በመስጠት እና በመግለጽ ላይ ትኩረቱን ያደርጋል፣ዝርዝር በሆኑ ሰዋስዋዊ ንድፈ ሀሳቦች ላይ ይመሰረታል፡፡ እንዲሁም በተማሪዎች ላይ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየት ጥረት ያደርጋል፡፡

ሰዋስውን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ከሚውሉ የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የመማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥም የሚቀርቡ ይዘቶች በሚፈለገው መልኩ ተመርጠው የተዘጋጁና የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ Breen and Candlin (1987) እንደሚገልጹት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት በዋነኝነት ሊዘጋጁ የቻሉት ለምን ዓላማ ነው? በውስጥ ያካተቷቸው የትምህርት ይዘቶች ምን ዓይነት ናቸው? የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ለማሳደግ የሚያደርጉት እገዛ እንዴት ይገለጻል? ሲዘጋጁ የተማሪዎችን ፍላጎት ማዕከል በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? እንዲሁም ትምህርት ይዘቶቹ በሚፈለገው መልኩ ተደራጅተዋል ወይስ አልተደራጁም? ወዘተ… የሚሉት ጥያቄዎች በቅድሚያ ተገቢ የሆነ መልስ ሊያገኙ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ስኬታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያደርሱ መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሰው የመማሪያ መጽሐፍት ብቃት ማነስ እንደሆነ Sheldon (1988) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሲባል ግን ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችል አብሮ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህም መማሪያ መጽሐፍት የሚታዩባቸውን ችግሮች ለመቀነስ የመማሪያ መጽሐፍቱን

በየጊዜው ማሻሻል አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ Sheldon (1988) አገላለጽ የመማሪያ መጽሐፍት አንድ ጊዜ ተዘጋጅተው የሚቆሙና ለረዥም ጊዜ አግልግሎት እንዲሰጡ የሚደረጉ ሳይሆን፤ በየጊዜው ጥንካሬያቸው እና ድክመታቸው እየተለየ እንደተማሪዎቹ ማንነት ማሻሻልን የሚጠይቁ እና ለውጠ ግዙ (Flexible) መሆን እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳሉ ፡፡

በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች የሚቀርቡበት እና የሚደራጁበት የራሳቸው የሆነ መንገድ አለ፡፡ ይህም የተማሪዎችን ማንነት ባገናዘበ መልኩ የትምህርቱ ሂደት ተጠይቃዊ የሆነ አደረጃጀትን የሚከተልና አቀራረቡም በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተቃኘ መሆን እንደሚኖርበት የሚያመለክት ነው፡፡ Larsen Freeman (1991)፣ Harmer (1991) እና Batstone (1994) እና Thornbury (2001) እንደሚያስረዱት የሰዋስው ማቅረቢያ መንገዶች ተብለው የሚታወቁት ጥቅል ቀደም እና ዝርዝር ቀደም እንዲሁም ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር ናቸው፡፡

ጥቅል ቀደም አቀራረብ መነሻ የሚያደርገው ጥቅል ዕሳቤዎችን ሲሆን፣ በመቀጠልም ዝርዝር የሆኑ ሰዋስዋዊ ጉዳዮች ተከትለው እንዲቀርቡ የሚደረግበት ነው፡፡ በዚህ የአቀራረብ ዘዴ የተመረጠው ሰዋስዋዊ ይዘት አውዳዊ በሆነ መልኩ ለተማሪዎቹ ከቀረበ በኋላ፣ የቀረበላቸውን መሰረት አድርገው መልመጃዎችን በተለያየ መንገድ እየሠሩ የሚሄዱበትን መንገድ ይፈጥራል፡፡ Fischer (1979) እንደሚያስረዱት በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች ጥቅል ቀደም አቀራረብን የሚከተሉ ከሆነ ተማሪዎቹ ተጠይቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል የሰዋስው ዕውቀትን በጊዜ ሂደት እንዲለዩ ያስችላቸዋል፡፡ ሆኖም ግን እንደ Shaffer (1989) አገላለጽ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰዋስውን ጥቅል ሀሳብ በቅድሚያ ተረድተው፣ በኋላ ተከትለው የሚመጡትን ዝርዝር ጉዳዮች በተገቢው መልኩ ያከናውናሉ ማለት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ለትምህርቱ ሂደት እንደዓላማ የተያዘውን ዋና ጽንሰ ሀሳብ (ጥቅል ሀሳብ) በሚፈለገው መልኩ በቅድሚያ የማይረዱት ከሆነ በዝርዝር መሥራት የሚጠበቅባቸውን ልዩ ልዩ ምሳሌዎች በተገቢው መልኩ ሊለዩት ስለማይችሉ ነው በማለት አቀራረቡን ይተቻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Thornbury (2001) እንደሚገልጹት ጥቅል ቀደም አቀራረብ በአሁኑ ሰዓት ቋንቋን ለመማር ከሚኖር ዓላማ አንጻር ሲታይ ተመራጭነቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ሰዎች ቋንቋን መማር የሚፈልጉት ለቃላዊ ተግባቦት በመሆን እና ይህ የአቀራረብ ዘዴ (ጥቅል ቀደም) ደግሞ ትኩረቱ መጻፍ ላይ እንጂ ንግግር ላይ ባለመሆኑ ጊዜው የሚፈልገውን የቋንቋ ትምህርት በዚህ መልኩ ለማቅረብ አመቺ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር ድክመት ይታይበታል፡፡

ዝርዝር ቀደም አቀራረብ ሁለተኛው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ የተመረጡትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች (ህግጋት) አንድ በአንድ ምሳሌዎችን በማሳየት ለተማሪዎቹ ካቀረብን በኋላ፣ ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን በተለያዩ መንገዶች እየሠሩ፣ በሂደት የሰዋስው ህግጋቱን በራሳቸው እንዲደርሱባቸው የሚደረግበት ነው (Nunan 1991)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ Brown (2000) ይህን ሀሳብ እንደሚያጠናክሩት ዝርዝር ቀደም የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎቹ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ህግጋትን የመመስረት እና የመፍጠር ዕድል እንዲኖራቸው ያስችላል፤ጥልቅ የሆነ ጽንሰ ሀሳቦችን በስፋት እንዲያገኙ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡እንዲሁም ከተለምዷዊ የቋንቋ ለመዳ ሂደት ጋር የሚጣጣም በመሆኑ፣ ተማሪዎቹ ደረጃ በደረጃ የቋንቋ ህግጋትን እንዲያዳብሩ መንገድ ያሳያቸዋል፡፡

በሌላ በኩል Omaggio (1986) እንደሚገልጹት በሰዋስው ትምህርት ሂደት አቀራረቡን ጥቅል ቀደም ወይም ዝርዝር ቀደም ለማድረግ፣ የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ይወስናሉ፡፡ ይኸውም፡- ቀለል ያሉ ሰዋስዋዊ ህግጋት ከሆኑ፣ የትምህርቱ ሂደት ከዝርዝር ወደጥቅል የሚሄድ አቀራረብን ቢከተል የተሻለ ነው፡፡ በሌላ በኩል ውስብስብ የሆኑ ሰዋስዋዊ ህግጋት ከሆኑ ደግሞ አቀራረቡ ከጥቅል ወደዝርዝር ቢሆን ይመረጣል፡፡
ከላይ ከቀረቡት ከሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች በተጨማሪ Batstone (1994) ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር በሚል ከፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ እንደ Batstone (1994) አገላለጽ ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመማር ማስተማሩ ሂደት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ለሰዋስዋዊ ህግጋት ወይም ለመዋቅር ነው፡፡ ስለሆነም በመማር ማስተማሩ ሂደት ሰፊ ሽፋን የሚሰጠው ለሰዋስዋዊ ህግጋት ወይም ለመዋቅር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ፣ ተማሪዎቹ ከድምጽ ጀምሮ ቃላትን እና ዓ.ነገሮችን እንዲለዩ ይደረጋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ የአቀራረብ፣ ከአገባብ ይልቅ ተማሪዎቹ የቋንቋውን መዋቅራዊ ህግጋትን እንዲተነትኑ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ሂደት ተኮር አቀራረብ ሁለተኛው ነው፡፡ አቀራረቡም የተመረጡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መልዕክትን በሚያስተላልፉ ወይም ተግባቦታዊ የሆነ አካሄድን በተከተለ መልኩ መቅረብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የአቀራረብ ስልት የትምህርቱ ሂደት አውዳዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብ ሲሆን፣ ተማሪዎቹም ተግባቦታዊ የሆኑ ተግባራት ላይ በማተኮር የቋንቋውን አጠቃቀም በጥልቀት እንዲፈትሹ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥርላቸዋል (Batstone 1994) ፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን አደረጃጀታቸውን ለመፈተሽ እንደመስፈርት ሆነው የሚነሱ መለኪያዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ተከታታይነት ነው፡፡ ይህም በአንዱ የክፍል ደረጃ የተካተተው ይዘት ቀጣይ የክፍል ደረጃ ላይ ተጠይቃዊ በሆነ መልኩ በማስገባት ማደራጀት እንደሚያስፈልግ የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይነት የሚለው የማደራጃ መስፈርት የሚያመለክተው በተለያየ የትምህርት (የክፍል) ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ወይም ይዘት እንደየክፍል ደረጃቸው መጥኖ መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ከሰዋስው የትምህርት ይዘቶች ውስጥ በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ስለሚኖሩ ባለቤት፣ ተሳቢ እና ማሰሪያ አንቀጽ የተመለከተ ተካቶ ቢቀርብ፤ በአስራ አንደኛ ክፍልም ይሁኑ ይዘት ጠለቅ ባለ መልኩ እንዲካተት ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎቹ ካላቸው የቀደመ ዕውቀት በመነሳት በትምህርቱ ሂደት ጥልቅ ዕውቀትን እንዲጨብጡ ያስችላቸዋል (Tyler 1949)፡፡ ይህንንም ሀሳብ Nunan (1988) እንደሚያጠናክሩት ተመሳሳይ የሆኑ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሳይዘበራረቁ ወይም ሳይቆራረጡ በየክፍል ደረጃዎቹ እንደተማሪዎቹ ማንነት ተሳስረው መሄድ የሚችሉ ከሆነ፣ የተማሪዎቹ ግንዛቤ በሂደት እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው የአደረጃጀት መለኪያ ተለጣጣቂነት ነው፡፡ Tyler (1949) ተለጣጣቂነትን በተመለከተ ሀሳባቸውን እንደሚያስቀምጡት፣ ተመሳሳይ የሆኑ የትምህርት ይዘቶች በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተለያየ አቀራረብ ተደጋግመው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የትምህርት ይዘቶቹ በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ ተደጋግመው በሚቀርቡበት ጊዜ ግን ስፋታቸው እና ጥልቀታቸው በተለያየ መንገድ ሊደራጁ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የመማሪያ መጽሐፍት መደራጀት ከቻሉ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ተመሳሳይ የትምህርት ይዘቶችን በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ማግኘት የሚችሉ በመሆኑ ይዘቱን በጥልቀት እንዲረዱት አስተዋጽኦ ያደርግላቸዋል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ አውድ ላይ ተመስርተው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ባለው መልኩ የተጠኑ ጥናቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ሀዋዝ (2000) በአዲስ አበባ እና አማራ ክልል አንደኛ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ የተገኘውም ውጤት ፣ በሁለቱም ክልሎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ መርሆችን አልሞ ያለመተግበር፣ የጽንሰ ሀሳብ፣ የአርትኦት እና ከመርሃ ትምህርቱ የመውጣት ችግሮች እንደሚስተዋሉ አሳይቷል፡፡

ሁለተኛው የእምሻው (2005) ጥናት ሲሆን፣ ከ1968 እስከ 2004ዓ.ም ድረስ ያሉ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን የፈተሸ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም እንደሚያሳየው በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከጥቅል ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደጥቅል፣ እንዲሁም በውጤት ተኮር እና በሂደት ተኮር የቀረቡ ቢኖሩም አቀቀራረባቸው ከስህተት የጸዳ እንዳልሆነ ጠቁሟል፡፡

ሶስተኛው ሁሴን (2012) ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጁት የ5ኛ እና የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ነው፡፡ በጥናቱም በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ሲቀርቡ በ6ኛ ክፍል ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች ግን ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የቀረቡ ይዘቶች እንደሌሉ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ በሌላ መልኩ በሁለቱም መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰፊ ድርሻ እንደተሰጣቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ በአንጻሩ ከአደረጃጀት አኳያ በሁለቱም መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ በአብዛኛው ተከታታይነታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

የመጨረሻው ጌታሁን(2016) "የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት ይዘት እና አቀራረብ ፣ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁ ከ5-8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ናሙናነት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናቱም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከአቀራረብ አንጻር በአብዛኛው ከዝርዝር ወደጥቅል እንዲሁም ጥቂት ይዘቶች ብቻ ከጥቅል ወደዝርዝር እንደቀረቡ ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም ከሂደት ተኮር ይልቅ፣ ውጤት ተኮርን መሰረት በማድረግ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ እንደቀረቡ የጥናቱ ውጤት ያመልክታል፡፡ በሌላ በኩል ከተከታታይነት እና ከተለጣጣቂነት አንጻር በአብዛኛው የተሻሉ ቢሆንም፣ የታዩ ችግሮች እንዳሉ የተጠቆመ ሲሆን፣ ከትክክለኝነት አንጻርም እንዲሁ ችግር እንደሚስተዋል በጥናቱ ለማሳየት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት አራት ጥናቶች መገንዘብ የሚቻለው፣ የጥናት ግኝቶቻቸው የተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ ለአብነት ያሀል ጌታሁን (2016) ከአቀራረብ አንጻር መማሪያ መጽሐፍቱ በአብዛኛው ከዝርዝር ወደጥቅል እንደቀረቡ ሲገልጹ፣ ሁሴን (2012) ደግሞ ከጥቅል ወደዝርዝር ሰፊ ሽፋን እንደተሰጣቸው ያመለክታሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው የውጤት ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአደረጃጀት አንጻርም በየጥናቶቹ የተገኙ ውጤቶች ሲታዩ አንዱ – ከአንዱ የተለየ ግኝት እንዳለው ነው፡፡ በሌላ መልኩ የጥናት ውጤቶቻቸው ልዩነት ከማሳየት ባሻገር በየጥናቶቻቸው ያተኮሩባቸው መማሪያ መጽሐፍት አንዳቸው ከሌላቸው ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍት ላይ ጥናታቸውን ሲያደርጉ አንዳንዶቹ ደግሞ ቀደም ባለው ስርዓተ ትምህርት ስራ ላይ በዋሉት መማሪያ መጽሀፍት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም በአራቱም ጥናቶች ውስጥ ባልተጠናው የ11ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱም የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎችን አካቷል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸው ምን ይመስላል?
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀታቸው እንዴት ይታያል?

## 2. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በ2004ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸው እና አደረጃጀታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን፣ በውስጡም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ያደርጋል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸውን መፈተሽ፤
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀታቸውን መመርመር፤

## 3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡

- የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እና አደረጃጀታቸውን በሚመለከት ምሁራን ከሚያነሷቸው ንድፈ ሀሳቦች አንጻር የተቃኙ መሆን–አለመሆናቸውን እንዲገነዘቡ እና በቀጣይ ለሚያዘጋጇቸው ወይም ለሚያሻሽሏቸው መጻህፍት እንደግብዓት በመሆን ሊያገለግላቸው ይችላል፡፡
- ወደፊት ለሚደረጉ ቀጣይ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 4. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ንድፉም ገላጭ ጥናት ላይ ተመስርቷል፡፡ በጥናቱ ውስጥም በዋነኝነት እንደመረጃ ምንጭነት የተወሰዱት በ2004ዓ.ም ተሻሽለው የወጡት የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና መርሀ ትምህርት ሲሆኑ፣ ከዚህም በተጨማሪ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና መርሀ ትምህርት ፣ ለጥናቱ በውስን ደረጃ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡ የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና በውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በአላማ ተኮር የናሙና ስልት እንዲመረጡ ተደርገዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ላይ በቀጥታም እና በተዘዋዋሪ የተጠኑ ጥናቶች በመኖራቸው የተነሳ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት በ2004ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ማተኮሩ እና በዚህ መጽሃፍ ላይ የተጠና ጥናት አጥኚው ያላጋጠመው መሆኑ፣ የናሙና አይነቱ ዓላማ ተኮር እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተግባር ላይ የዋለው የሰነድ ፍተሻ ሲሆን፣ከአቀራረብ አንጻር ቅጹን ለማዘጋጀት Omaggio (1986) ፣ Brown (2000)፣ Thornbury (2001) እና Batstone (1994) ያነሷቸውን ሞዴሎች መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአደረጃጀት አንጻር Tyler (1949)፣ Nunan (1988)፣ Palma (1992) እና Sheldon (1988) ካነሷቸው ሞዴሎች በመነሳት የሰነድ ፍተሻ ቅጹ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ እነዚህም የተገኙ መረጃዎች በንዑሳን ርዕሶች እንዲከፋፈሉ ከተደረገ በኋላ፣ ምሁራን የሚያስቀምጧቸውን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

## 5. **የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ**

**ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በ2004ዓ.ም. ተሻሽሎ የታተመው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረባቸው እና አደረጃጀታቸውን መፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ የተገኙ መረጃዎችን ምሁራን ከሚያስቀምጧቸው ንድፈ ሀሳቦች በመነሳት ከዚህ በታች በቀረበው መልኩ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ በቀጥታ ወደትንታኔው ከመገባቱ በፊት ግን ለመነሻ ያህል ስለመማሪያ መጽሐፉ አጠር ያለ ዳራዊ ዳሰሳ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

## 5.1 **በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተደረገ አጠቃላይ ዳሰሳ**

**የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በ2004ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበ ሲሆን፣ በውስጡም አስር ምዕራፎችን አካቶ ይዟል፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥም የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የማዳመጥ ፣ የሥነ ጽሑፍ እና የሰዋስው ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ መማሪያ መጽሐፉ ተሻሽሎ ከመውጣቱ ጋር በተያያዘ፣ ከዚህ ቀደም ከተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት አንጻር ሲታይ ይዘቶቹ የተለየ የአቀራረብ ስልትን የተከተሉ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም ከዚህ ቀደም በነበሩት የመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ያልተካተቱ፣ ሆኖም ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ትኩረት ከተሰጠባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡**

- **በየምዕራፎቹ ውስጥ የማጠቃለያ ጽሑፎች መቅረባቸው እና ይህንንም ተከትለው የክለሳ ጥያቄዎች መካተት መቻላቸው፤**
- **እንዲሁም ተማሪዎቹ በየምዕራፉ ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ይዘቶችን ምን ያህል እንደተረዷቸው የሚለዩበት የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጾች መቅረባቸው በዋነኝነት መማሪያ መጽሐፍቱ ትኩረት የሰጡባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡**

## 5.2 **የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር**

**ቀደም ሲል በጥናቱ ዳራ ላይ ለማንሳት እንደተሞከረው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በሁለት ፈርጅ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ የመጀመሪያው ጥቅል ቀደም እና ዝርዝር ቀደም አቀራረብ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ ቢዚህ የውጤት ትንተና ሂደትም ምሁራኑ ከሚያነሷቸው ንድፈ ሀሳቦች በመነሳት መማሪያ መጽሐፉ ምን እንደሚመስል በተናጠል ለመፈተሽ ይሞከራል፡፡**

### 5.2.1 **ጥቅል ቀደም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ**

- **ጥቅል ቀደም አቀራረብ መነሻ የሚያደርገው ሰዋስዋዊ ህግጋትን ሲሆን፣ በመቀጠል ምሳሌዎቹ ተከትለው ይመጣሉ፡፡ ከዚህም አኳያ በአስራ አንደኛ ክፍል የቀረበው የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ይዘት ሲታይ፣ ይህን በተመለከተ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- በገጽ 143 የቃል ክፍሎችን ሙያ በተመለከተ የሚከተለው ጥያቄ ሰፍሮ ይገኛል፡፡**

> **ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ክፍል አራት ስለቃል ክፍሎች ሙያ የሰፈረውን ማስታወሻ በማንበብና የተማራችሁትን በማስታወስ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ዓ.ነገሮች ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን ከነሙያቸው ዘርዝሩ፡፡**

**ከላይ የቀረበው የጥያቄ መመሪያ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ ስለቃል ክፍሎች ሙያ የተመለከተውን ይዘት ከተረዱ በኋላ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች በዝርዝር እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው በመሆኑ የተነሳ የጥያቄው አቀራረቡ ከጥቅል ወደዝርዝር አካሄድን የተከተለ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ዓይነት አቀራረብ የተቀመጡ የሰዋስው ይዘቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- **ገጽ 22 ደምጸ ልሳናት፣ ገጽ 24 ስነ ድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ፣ ገጽ 25 ቀለማዊ አጻጻፍ፣ ገጽ 50 የቃል ክፍሎች ሙያ፣ ገጽ 66 እና 68 የእርባታና የምስረታ ቅጥያ፣ እንዲሁም ገጽ 192 የቃል ክፍሎች ሙያ ከጥቅል ወደ ዝርዝር አቀራረብን የተከተሉ ናቸው፡፡**
-

### 5.2.2 ዝርዝር ቀደም የሰዋስው የትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ

ይህ አቀራረብ ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን በቅድሚያ በማሳየት በመቀጠል ወደህግጋቱ በመምጣት ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከዝርዝር ወደጥቅል አቀራረብ ተዘጋጅተው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች እንዳሉ ለመለየት የተቻለ ሲሆን፣ ለዚህም እንደማሳያ የሚከተለውን ምሳሌ መመልከት ይቻላል፡፡

ገጽ 121፡- ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ የሰጣችሁትን ፍቺ ግልጽ የሚያደርጉ ዓረፍተነገሮችን ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡-

| ተ.ቁ | ቃል | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|---|
| 1 | አልሄደም | ፈቀቅ አላለም | ተራምዷል |

ሀ. ትላንት የጀመርነው ሥራ ፈቀቅ አላለም፡፡
ለ. ትላንት የጀመርነው ሥራ ተራምዷል፡፡

ከላይ ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው፣ ተማሪዎቹ በተቀመጠላቸው አንድ ምሳሌ በመነሳት የተሰጣቸውን ቃላት በዝርዝር ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺያቸውን እንዲለዩ እና ዓ.ነገሮችን እንዲሠሩባቸው የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይኸውም ስለተመሳሳይና ስለተቃራኒ ፍቺ እንዲሁም ስለዓ.ነገር አመሰራረት በሂደት ወደአንድ ፅሳቤ እንዲመጡ የሚያስችል የጥያቄ አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም ዝርዝር ቀደም አቀራረብ፣ ተማሪዎቹ ዝርዝር ጉዳዮችን ተረድተው ወደአንድ መሰረታዊ ጉዳይ እንዲመጡ የሚያስችል በመሆኑ የሰዋስው ይዘቱ ከዝርዝር ወደጥቅል አካሄድን የተከተለ ነው፡፡ በተመሳሳይ በዚሁ የአቀራረብ ስልት የተቃኙ ሌሎች የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ያሉ ሲሆን፣ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ገጽ 25 መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት፣ ገጽ 26 የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ በዓ.ነገር ማሳየት፣ ገጽ 46 በተቃራኒ ፍቺ ዓ.ነገር መስራት፣ ገጽ 84 በዓ.ነገር ውስጥ ለቃላት ፍቺ መስጠት ፣ ገጽ 85 በዓ.ነገሮች ውስጥ የቃል ክፍሎችን መለየት፣ እንዲሁም ገጽ 144 የዕርባታ ምዕላድ በተውላጠ ስሞች ማሳየት የሚሉት የሰዋስው ይዘቶች ከዝርዝር ወደጥቅል አቀራረብን የተከተሉ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ በሰዋስው ትምህርት ሂደት አቀራረቡን ጥቅል ወይም ዝርዝር ቀደም ለማድረግ፣ የሚቀርበው ሰዋስዋዊ ይዘት ይወስነዋል፡፡ ይኸውም ቀለል ያሉ ሰዋስዋዊ ህግጋት ከሆኑ፣ ከዝርዝር ወደጥቅል የሚሄድ አቀራረብን መከተል የሚኖርባቸው ሲሆን፤ ውስብስብ የሆኑ ሰዋስዋዊ ህግጋት ከሆኑ ደግሞ አቀራረቡ ከጥቅል ወደዝርዝር ቢሆን ይመረጣል፡፡ ከዚህም አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው ይዘቶች በአብዛኛው አቀራረባቸው ተገቢ እንደሆነ ለመለየት የተቻለ ሲሆን፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ግን ችግር እንደሚስተዋል ለመለየት ተችሏል፡፡

- ገጽ 85 በዓ.ነገሮች ውስጥ የቃል ክፍሎችን መለየት፤
- እንዲሁም ገጽ 144 በዓ.ነገር ሙያ ውስጥ አድራጊ፣ ተደራጊ እና አስደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ መለየት የሚሉት ጥያቄዎች፣ ስለሰዋስዋዊ ህግጋቱ የመምህሩን ዝርዝር ማብራሪያ የሚፈልጉ ሆነው ነገር ግን ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሳይቀመጥላቸው ተማሪዎቹ ከተቀመጠላቸው ምሳሌ በመነሳት ብቻ እንዲሠሯቸው መቅረባቸው ተገቢነት የሌለው እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከጥቅል ወደዝርዝር እና ከዝርዝር ወደጥቅል በሚል አቀራረብ በተመጣጣኝ መልኩ የቀረቡ ቢሆንም፣ አንዳንድ ይዘቶች ግን ከዝርዝር ወደጥቅል መቅረብ ሲገባቸው፣ መቅረብ እንዳልቻሉ (ከጥቅል ወደዝርዝር እንደቀረቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የተገኘው ውጤት ቀደም ሲል ከተጠኑ ጥናቶች መካከል ጌታሁን (2016) በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ከዝርዝር ወደጥቅል የቀረቡ ናቸው ከሚል የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ውጤት አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁሴን (2012) የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ትኩረት ያደረጉት ከጥቅል ወደዝርዝር ከሚል የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ውጤት ሊገኝ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ሀዋዝ (2006) አቀራረቦቹ መርሆችን አልሞ ያለመተግበር ከሚል የጥናት ግኝት እና እምሻው (2005) የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከጥቅል ወደዝርዝር እንዲሁም ከዝርዝር ወደጥቅል የቀረቡ ቢሆኑም ከስህተት የጸዱ አይደሉም በሚል ካስቀመጡት የጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 5.2.3 ከውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንጻር

በውጤት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ የተቃኘ የትምህርት ሂደት ከመነሻው እስከመድረሻው ትኩረት የሚያደርገው የቋንቋው መዋቅር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦት አውድ ቃኝቶ ከማቅረብ ይልቅ የቋንቋውን ንዑስ አሃድ (ህግጋት) ተማሪዎቹ እየተነተኑ እንዲማሩ እድል የሚፈጥር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በተከተለ መልኩ የተቀመጡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዳሉ ለመለየት ተችሏል፡፡ ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችል ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ገጽ 65፡- በሚከተለው ሰንጠረዥ የዕርባታና የምስረታ ቅጥያዎች ያረፉባቸው ቃላት ተሰጥተዋል፡ ፡ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ቅጥያ ምዕላድ | የቅጥያ ምዕላድ አይነት | የቅጥያ ምዕላድ ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መንፈሳዊ | -አዊ | የምስረታ ቅጥያ | ቅጽል መስራችነት |
| 2 | ትምህርት ቤታችን | -አችን | የርባታ ቅጥያ | አገናዛቢ መስራችነት |
| 3 | ዝናባማ | | | |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ሰዋስዋዊ መዋቅር መሰረት የተለያዩ ቃላት በውስጣቸው የያዙትን ምዕላድ እንዲለዩ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም በቋንቋው መዋቅር ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ የሰዋስው ትምህርቱ አቀራረብ ውጤት ተኮር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመማሪያ መጽሐፉ የሚከተሉት ይዘቶች በውጤት ተኮር አቀራረብ ተሰናድተው የቀረቡ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ገጽ 22፡- መካነ ፍጥረት እና ባህርየ ፍጥረት መለየት
- ገጽ 24-25፡- ድምጸ ልሳናዊ እና ቀለማዊ አጻጻፍ
- ገጽ 65፣ 68፣ 144 እና 160 ፡- የእርባታ እና የምስረታ ቅጥያዎች
- እንዲሁም ገጽ 85፡- በዓ.ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን መለየት የሚሉት የሰዋስው ይዘቶች ውጤት ተኮር አቀራረብን የተከተሉ ናቸው፡፡

### 5.2.4 ከሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንጻር

ሂደት ተኮር አቀራረብ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተግባቦታዊ አውዶች ጋር ተቀናጅተው መቅረብ እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በዚህ ትምህርት ሂደት የሰዋስው ይዘቶች ተነጣጥለው ከመቅረብ ይልቅ አውድን በሚያሳይ መልኩ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ ተተኳሪ በሆነው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን የተከተሉ ይዘቶች ለመለየት የተቻለ ሲሆን፣ እንደምሳሌም የሚከተለውን መመልከት ይቻላል፡፡

ቀጥሎ በቀረቡላችሁ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡-
ወለብላባ ሰው የሌላውን ሐሳብ ለማዳመጥ አይሞክርም
ተመሳሳይ፡- ለፍላፊ፣ምላሰኛ
ተቃራኒ፡- ዝምተኛ

ከላይ የቀረበው ምሳሌ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎቹ በዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በአውድ ውስጥ በማስገባት ፍቺያቸውን እንዲለዩ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህም ደግሞ ቃላትን ከአውድ ውስጥ ተማሪዎቹ እንዲለዩ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ አቀራረቡ ሂደት ተኮር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሂደት ተኮር በሆነ የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ሌሎች የሰዋስው ይዘቶች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ገጽ 25፣ 46 ፣ 84 እና 122 የቃላትን ፍቺ መለየት
- እንዲሁም ገጽ 143 በዓ.ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መለየት የሚሉት ሂደታዊ የአቀራረብ ስልትን የተከተሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የተቃኙ የሰዋስው ይዘቶች ከሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት በበለጠ ሁኔታ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መቅረብ እንደቻሉ ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ውጤት ሁሴን (2012) ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከውጤት ተኮር በተሻለ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ከሚለው የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ሲሆን፣ጌታሁን (2016) ከሂደት ተኮር ይልቅ ውጤት ተኮር ሰፊ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ከሚል የጥናት ግኝታቸው ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተግኝቷል፡፡ በተመሳሳይ ሀዋዝ (2000) በሁለቱም ክልሎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆችን አልሞ ያለመተግበር፣ ከሚለው የጥናት ውጤት እንዲሁም እምሻው (2005) በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በውጤት ተኮር እና በሂደት ተኮር የቀረቡ ቢኖሩም አቀቀራረባቸው ከስህተት የጸዳ እንዳልሆነ ከጠቆሙት ጥናት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 5.3 ከመማሪያ መጽሐፉ አደረጃጀት አንጻር

### 5.3.1 ከተከታታይነት አንጻር

ተከታታይነት አንዱ የመማሪያ መጽሃፍ አደረጃጀት መለኪያ መስፈርት ሲሆን፣ ተመሳሳይ የሰዋሰው ይዘቶች እንደየክፍል ደረጃቸው ተመጥነው መቅረብ እንደሚኖርባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናቱ የመረጃ ምንጭ የሆነውን የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ በውስጡ ያካተታቸውን የሰዋስው ይዘቶች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ መደራጀቱን ለማጤን የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል፡፡

በዚህም መሰረት የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች፣ ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ከቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች ላይ ተመስርተው የመቅረባቸው ሁኔታ ሲታይ፣ በተወሰነ ደረጃ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በተመሳሳይ የትምህርት ይዘት ገብተው፣ አቀራረባቸው የተማሪዎችን ደረጃ ባገናዘበ አኳያ የተደራጁ የትምህርት ይዘቶች እንዳሉ ለመለየት ተችሏል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት፣ የቃላት ዕርባታና ምስረታ፣ የድምጽ መጥበቅና መላላት እንዲሁም ምዕላድን መተንተን በሁለቱም መማሪያ መጽሐፍት ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑ ነው፡፡ እነዚህም ይዘቶች፣ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ከመካከተታቸው ባሻገር አቀራረባቸው የተለያየ ሆኖ ይታያል፡፡ ለምሳሌ፡- በአስራ አንደኛ ክፍል ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት በሚለው ይዘት ውስጥ ተማሪዎቹ በቃል ደረጃ የተሰጣቸውን ፍቺ በዓ.ነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቅ ሲሆን፣ በአስረኛ ክፍል ውስጥ ግን በቃል ደረጃ የተቀመጡትን ፍቺያቸውን ብቻ እንዲናገሩ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው በአስራ አንደኛ ክፍል ውስጥ የቀረበው የሰዋስው ይዘት ከተከታታይነት አንጻር በተገቢው ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረብ እንደቻለ ነው፡፡

በሌላ በኩል አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች በአንዱ የክፍል ደረጃ ትኩረት ተሰጥቷቸው በሌላኛው የክፍል ደረጃ ግን በይዘትነት መካተት አለመቻላቸው እንደትልቅ ድክመት ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም፣ በቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት፣ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት/ሀረጋት፣ የዓ.ነገር ዓይነቶች፣ የዓ.ነገር ስልቶች፣ ተራና ውስብስብ ዓ.ነገሮች፣ ሀረጋትን መመስረት፣ እንዲሁም ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን አቀናጅቶ ቃልን መመስረት፣ የሚሉት ይዘቶች በአስረኛ ክፍል ውስጥ ተካተው፤ በአስራ አንደኛ ክፍል ውስጥ በተለየ አቀራረብ መቅረብ ሲገባቸው ያልተካተቱ ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታም፣ በአስራ አንደኛ ክፍል ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች አብዛኞቹ በቃል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ሲሆኑ፣ የአስረኛ ክፍል ደግሞ በሀረግ እና በዓ.ነገር ደረጃ የተቀመጡ የሰዋስው ይዘቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች፣ ከአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ይዘቶች ጋር በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም፣ አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች ግን ቀጣይነት እና ተጠይቃዊ በሆነ መልኩ የመደራጀታቸው ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.3.2 ከተለጣጣቂነት አንጻር

ተለጣጣቂነት፣ ተመሳሳይ የሆኑ የትምህርት ይዘቶች በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተለያየ አቀራረብ ተደጋግመው መቅረብ እንደሚኖርባቸው የሚያመልክት ነው፡፡

ከዚህም አኳያ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች የተላጣጣቂነት ሁኔታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ የተቻለ ሲሆን፣ በዚህም መሰረት ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የተላጣጣቂነት ደረጃቸውን የጠበቁት የትምህርት ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ አንድ፡- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንጻር ተደራጅተው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች

| ተ.ቁ | የትምህርት ይዘቶች | የሚገኙበት ምዕራፍ |
|---|---|---|
| 1 | ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | ምዕራፍ ሁለት ፣አራት እና ስድስት |
| 2 | የቃል ክፍሎች ሙያ | ምዕራፍ ሁለት፣ አራት፣ ሰባት እና አስር |
| 3 | የዕርባታ እና የምስረታ ምዕላዶች | ምዕራፍ ሶስት፣ ሰባት እና ስምንት |

ከላይ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይዘቶቹ በተለጣጣቂነት ደረጃ እንደተደራጁ የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህም የትምህርት ይዘቶች በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ የተደራጁት የተለያየ አቀራረብን ተከትለው ነው፡፡ ለዚህም እንደማሳያ በተራ ቁጥር አንድ የቀረበውን ይዘት ብንመለከት፡- በምዕራፍ ሁለት፣ አራት እና ስድስት ይዘቱ ተለጣጥቆ ሲቀርብ፣ ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚጠይቅ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ ይኸውም በምዕራፍ ሁለት ላይ ተማሪዎቹ ለቀረበላቸው ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ከሰጡ በኋላ ዓ.ነገር እንዲሠሩባቸው የሚጠይቅ ሲሆን፣ በምዕራፍ ሶስት ደግሞ በዓ.ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው፤ በተጨማሪም በምዕራፍ ስድስት ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ቃላት የፍቺ ልዩነት የሚያመጡ ከሆነ፣ ፍቺያቸውን እንዲለዩ የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይም አደረጃጀቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች እንዳሉ ሁሉ ሳይደራጁ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች እንዳሉ ለመለየት ተችሏል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበውም ሰንጠረዥ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንጻር ሳይደራጁ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶችን የሚያመለክት ነው፡፡

ሰንጠረዥ ሁለት፡- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንጻር ሳይደራጁ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች

| ተ.ቁ | የትምህርት ይዘቶች | የሚገኙበት ምዕራፍ |
|---|---|---|
| 1 | አናባቢና ተናባቢ ድምጸ ልሳናት መለየት | ምዕራፍ አንድ |
| 2 | ቀለማዊ አጻጻፍ | ምዕራፍ አንድ |
| 3 | ቃላትን በድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ መተንተን | ምዕራፍ ሶስት |
| 4 | የቅጥያ ምዕላዶች ተግባር | ምዕራፍ ስድስት |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው፣ አናባቢና ተናባቢ ድምጸ ልሳናት መለየት፣ ቀለማዊ አጻጻፍ፣ ቃላትን በድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ መተንተን እና የቅጥያ ምዕላዶች ተግባር የሚሉት የሰዋስው ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተደራጅተው እንዳልቀረቡ ነው፡፡ በመሆኑም ጌታሁን (2016) ከተከታታይነት እና ከተለጣጣቂነት አንጻር በእብዛኛው የተሻሉ ቢሆንም የታዩ ችግሮች እንዳሉ ከጠቆሙት የጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሲሆን፣ ሁሴን (2012) ከአደረጃጀት አኳያ በሁለቱም መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ በአብዛኛው ተከታታይነታቸውን የጠበቁ ናቸው ከሚለው የጥናት ግኝታቸው ጋር አንጻራዊ የሆነ መደጋፍ እንዳለው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

# 6. መደምደሚያ እና አስተያየት

## 6.1 መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል አጠቃላይ የሆነ ግምገማ ማካሄድ ነው፡፡ ከዚህም ዓላማ በመነሳት የተለያዩ ምሁራን ስለትምህርት ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ በተመለከተ ያስቀመጧቸውን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ላይ ፍተሻ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ከተደረገውም ፍተሻ የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ በጥቅል ቀደም እና በዝርዝር ቀደም  ተዘጋጅተው እንደቀረቡ ለመለየት የተቻለ ሲሆን፤ ሆኖም በዝርዝር ቀደም ከቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ስለሰዋስዋዊ ህግጋቱ የመምህሩን ዝርዝር ማብራሪያ የሚፈልጉ ሆነው ነገር ግን ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሳይቀመጥላቸው ተማሪዎቹ ከተቀመጠላቸው ምሳሌ በመነሳት ብቻ እንዲሠሯቸው መቅረባቸው ተገቢነት የሌለው እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡

- በውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተቃኝተው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ በአብዛኛው ግን የሰዋስው ይዘቶቹ ውጤት ተኮር አቀራረብ ስልትን የተከተሉ እንደሆነ ለመለየት ተችሏል፡፡

- መማሪያ መጽሐፉ ከተከታታይነት አንጻር ሲታይ የተወሰኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መሰረት በማድረግ እንደተዘጋጁ ለመለየት የተቻለ ሲሆን፤ ከተለጣጣቂነት አንጻር ደግሞ ሲታይ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው ይዘቶች በተወሰነ መልኩ ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቢሆንም፤  የአደረጃጀት ቅደም ተከተል ላይ ችግር እንደሚስተዋል ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 6.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

በዚህ የጥናት ሂደት በተደረገው የሰነድ ፍተሻ  የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት እና አቀራረቦች ላይ የታዩ ጠናካራ እና ደካማ ጎኖችን ለመለየት ተችሏል፡፡  ጠንካራ ጎኖቹ እንዳሉ ሆነው፤ ከአደረጃጀት እና ከአቀራረብ አንጻር ለተስተዋሉ ችግሮች ግን መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት ነጥቦች በጥናቱ ሂደት ለተስተዋሉ ችግሮች በመፍትሄ ሀሳብነት የቀረቡ ናቸው፡፡

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ጥቅል ቀደም እና ዝርዝር ቀደም አቀራረብን ተከትለው መዘጋጀታቸው ተገቢነት ያለው ሆኖ፤ አቀራረባቸው ግን እንደይዘቶቹ ክብደት እና ቅለት ተዘጋጅተው መቅረብ ቢችሉ፤
- በውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተቃኝተው የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መቅረብ ቢችሉ ፤ ይኸውም፤ አውድን የሚፈልጉ የሰዋስው ይዘቶች በሂደት ተኮር አቀራረብ፤ እንዲሁም ቅርጽን መሰረት የሚያደርጉት በውጤት ተኮር የሰዋስው ተምህርት አቀራረብ ተቃኝተው ቢቀርቡ፤
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ አንዳንድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት ባለው መልኩ ለማደራጀት፣ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች ጥልቅ በሆነ መልኩ በመገንዘብ በአስራ አንደኛ ክፍል ውስጥ ማደራጀት ቢቻል፤
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶች የአደረጃጀታቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ ተለጣጣቂ ሆነው መቅረብ ቢችሉ፤
- በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለሰዋስው ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን በየጊዜው የሚወጡ ምርምሮችን መነሻ በማድረግ እንደተማሪዎቹ ማንነት ሥርዓተ ትምህርትን ሊያሻሽሉ ወይም ሊቀርጹ የሚችሉ አካላትን ማሳተፍ ቢቻል ለተከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

**ዋቢ ጽሑፎች**

**ሀዋዝ ወልደየስ፡፡**(2000)፡፡ **"በአዲስ አበባ ከተማ እና አማራ ክልል አንደኛ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት" በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት** (**ያልታተመ**)፡፡

**ሁሴን አደም፡፡** (2012)፡፡ **"ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጁት የ**5**ኛ እና የ**6**ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት" ጎንደር ዩንቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት** (**ያልታተመ**)፡፡

**ባየ ይማም፡፡** (2000)፡፡ **የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ ማ. ኃ. የተ. የግ. ማኅበር፡፡**

**ትምህርት ሚኒስቴር ፡፡**(2004)፡፡**አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ አስራ አንደኛ ክፍል፡፡ ዱባይ፣ አል-ጎሬር አታሚ ድርጅት፡፡**

_______፡፡(2004)፡፡ **አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ አስረኛ ክፍል፡፡ ዱባይ፣አል-ጎሬር አታሚ ድርጅት፡፡**

_______፡፡(2004)፡፡ **አማርኛ የመምህር መምሪያ አስራ አንደኛ ክፍል፡፡ ዱባይ፣አል-ጎሬር አታሚ ድርጅት፡፡**

______፡፡(2004)፡፡ **አማርኛ የመምህር መምሪያ አስረኛ ክፍል፡፡ ዱባይ፣አል-ጎሬር አታሚ ድርጅት፡፡**

**እምሻው ማሞ፡፡** (2005)፡፡ **"ለ**9**ኛ እና ለ**10**ኛ ክፍል በተዘጋጁት**(**ከ**1968-2004**ዓ.ም**) **የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ"፡፡ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት** (**ያልታተመ**)፡፡

**ጌታሁን አማረ ፡፡**(1990)፡፡ **ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡**

______ ፡፡(2016)፡፡ **የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት ይዘት እና አቀራረብ ፣ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁ ከ**5-**8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ናሙናነት፡፡ Journal of Ethiopian Studies , December, 2016, Vol. 49.**

Batstone, R. (1994). *Grammar.* Oxford: Oxford University Press.

Breen, M & Candlin, C. (1987). "Which materials? A consumers' and designers' guide" in Sheldon L (ed) ELT Textbooks and materials: Problems in evaluation and development ELT Docs . London: Modern English Publications.

Brown, D. (2000). *Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy. San Fransisco : San Fransisco State University.*

Fischer, R. A. (1979). "The inductive-deductive controversy revisited". *The Modern Language Journal.*

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar.* Longman: Longman.

_________ .(1991). *The Practice of English Language Teaching.* New York. Longman Ltd.

Larsen Freeman,D. (1991). " *Teaching Grammar" in Celce- Murcia, M (ed) Teaching English as a Second or Foreign Language.* Boston: Heinle Publishers.

Nunan, D. (1988). *Syllabus Design.* Oxford:Oxford University Press.

_________ .(1991). *Language Teaching Methodology A Textbook for Teachers.* London: Prentice Hall International LTD.

Omaggio, A. C. (1986). *Teaching Language in Context.* Heinle & Heinle.

Palma J.C. (1992). *Curriculum development system.* Philippines: National Book Store Inc.

Richards , J.C.& Schimdit, R.(2002). *Longman Dictionary of Language Teaching and Applied Linguistics.* London: Longman ltd.

Shaffer, C. (1989). "A Comparison of Inductive and Deductive Approaches to Teaching Foreign Languages". *The Modern Language Journal* 73:396-403

Sheldon, L.E. (1988). "Evaluating ELT Text Book and Materials" *ELT Journal* Vol. 42, No. 4

Thornburry, S. (2001). *How to Teach Grammar.* London: Pearson Education Limited England.

Tyler, J. (1949).*Basic Principles of Curriculum and Instruction.* Chicago: Chicago University Press.

Ur, P. (1988). *Grammar Practices Activities.* Cambridge: CUP.